## *ለማን እንታዘዝ?*

የሰው ልጅ በዚህ ዓለም እንዲኖር በተሰጠው ውስን የሕይዎት ዘመኑ ለማን መታዘዝ እንደሚገባው አውቆ ሕግና ትዕዛዝን ጠብቆ መኖር ነጻነትን የሚያጎናጽፍ ብቸኛ መንገድ ሲሆን፣ ለማን እንደሚታዘዙ ባለማወቅ ከሕግና ከሥርዓት ውጭ መኖር ግን ነጻነትን የሚያሳጣ አደገኛ ጉዞ ነው። አባታችን አዳም ለማን እንደሚታዘዝ ባለማወቅ የሰይጣንን የተሳሳተ መመሪያ በመቀበሉ ነጻነቱን አጥቶ የሰቆቃ ሕይወት መኖር ግድ ሆኖበታል። የሰው ልጅ በሕይወቱ ሊታዘዝላቸው የሚገባ ሁለት ወሳኝ ባለሥልጣናት አሉ። እነሱም፡-

***ሀ) ኅሊና (ኮንሳይንስ)***
***ለ) ቃለ እግዚአብሔር (አምላካዊ ሕግ) ናቸው።***

### *ሀ) ኅሊና (ኮንሳይንስ)*

ኅሊና ለሰው ልጅ በተፈጥሮ የተሰጠ ክፉና በጎውን ለመለየት የሚያስችል የማስተዋል ጸጋ ነው። ቅዱስ ጳውሎስ ይህን አስመልክቶ ሲናገር "በክርስቶስ ሆኜ እውነትን እናገራለሁ፤ አልዋሽምም፤ ሕሊናዬም በመንፈስ ቅዱስ ይመሰክርልኛል" (ሮሜ 9፡1) ይላል። አንድን አዲስ የተገዛ ማሽን ያለ ማኗል (መገለጫ) መገጣጠም እንደማይቻል ሁሉ የሰው ልጅም በተፈጥሮው አስተዋይ ኅሊና ባይኖረው ከእንስሳት ባልተለየም ነበር። ለኅሊናው የሚታዘዝ ክርስቲያን በዚህ ዓለም ላይ ሰዎች የሠሩት ሕግ ለእሱ ትርጉም የለውም። ምክንያቱም በወረቀት ላይ የሰፈረ ሕግ ያስፈለገበት ምክንያት ሰው ለኅሊናው መታዘዝ ባለመቻሉ ነውና። በወረቀት ላይ የሰፈረን ሕግ ተላልፈን ወንጀል ብንፈጽም ሕጉን የደነገገው ባለሥልጣን የራሱ አስፈጻሚ አካላት ስለ አለው ምስክር አቁሞ ለፍርድ ያቀርበናል፤ የሚገባንን ተመጣጣኝ ቅጣትም እናገኛለን። በተመሳሳይ ሁኔታ ቅዱስ ጳውሎስ "ሕሊናቸውን እያቆሰላችሁ ክርስቶስን ትበድላላችሁ" (1ቆሮ 8፡12) እንዳለው ክፉና በጎን መለየት የሚያስችለን ኅሊናችን ሚዛኑን ሳይስት (ሳይደፈርስ) ጤነኛ አእምሮ እያለን፣ ሰው አያውቅብንም ብለን በአእምሯችን የተሳለውን ውሳጣዊ የፈጥሮ ሕግ በመጋፋት ብንዋሽና ለማታለል ብንሞክር ኅሊናችን ራሱ ዳኛ፣ ራሱ መስካሪ ሆኖ እንደሚገባን ይቀጣናል።

### *የህሊና ቅጣት*

- ፈሪ፣ ደንጋጣና በራሳችን የማንተማመን ያደርገናል።
- በሰው ፊት ሞገሳችንን ያቀለዋል።
- በድብርት (ዲፕረሽን) እና በጭንቀት (አንዛይቲ) በሽታ እንድንሰቃይ ያደርገናል።
- የፈጸምነው ጥፋት ተመጣጣኝ ካሳ የማይገኝለት መሆኑን ስናውቅ ራሳችንን እንድናጠፋ (ሱሳይድ እንድናደርግ) ያስገድደናል።

በክርስቶስ ዘመን የነበሩ የሌላው ሰው በደል እንጅ የራሳቸው ጥፋት የማይታያቸው ጸሐፍትና ፈሪሳውያን ስታመነዝር ተገኘች ያሏትን ሴት በጌታ ፊት አቅርበው እንደ ሕጋቸው በድንጋይ ወግረው እንዲገድሏት የእሱን አወንታዊ ምልሽ ይጠብቁ ነበር። እሱ ግን "ከእናንተ ኃጢአት የሌለበት አስቀድሞ በድንጋይ ይውገራት አላቸው" አላቸው። "እነርሱም ይህን ሲሰሙ ሕሊናቸው ወቀሳቸውና ከሽማግሌዎች ጀምረው እስከ ኋለኞች አንድ አንድ እያሉ ወጡ" (ዮሐ 8፡8) በማለት የኅሊና ተግሳጽ ከባድ መሆኑን ወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ አስረግጦ ይነግረናል።

እዚህ ላይ ተደጋግሞ የሚነሳ አንድ መሠረታዊ ነጥብ አለ። ብዙ ጊዜ እግዚአብሔር የቀባቸው ካህናት ወይም እሱን እናገለግላለን ብለው በቅዱስ ማደሪያው ውስጥ በኃላፊነት የተመደቡና በሥጋና በደሙ የከበሩ ሰዎች በሩቅ ሆኖ እነሱን የሚመለከት ተራ ሰው የማይፈጽመውን ቁልጭ ያለ በደል ሲፈጽሙ ስናይ እግዚአብሔር በማደሪያው የለም ማለት ነው እንዴ! ብለን እንገረማለን፤ እናዝናለንም። ለዚህ ዋናው ምክንያት እነዚህ ሰዎች ከመጀመሪያው ወደ እግዚአብሔር ቤት ሲቀርቡ ለሥጋዊ ክብር (ማለት ለሹመት ወይም ለጥቅም) ብለው እንጅ መንፈሳዊ በረከትን ተመኝተው ባለመሆኑ ይወድቁና ይሰናከሉ ዘንድ ሰይጣን የተመኙትን ነገር በፍጥነት እንዳያገኙ መሰናክል ያበዛባቸዋል። በዚህም ምክንያት የተመኙትን ለማግኘት ሲሉ ከነርሱ የማይጠበቀውን በማድረግ ሕገ እግዚአብሔርን ይተላለፋሉ፣ የታመነባቸውንም ሕዝብ ያሳዝናሉ። የእነሱ ጉዳይ አንድ ጊዜ ሕዝብ ጆሮ ከገባ በኋላ የተወራ ቢወራ ደንታ አይሰጣቸውም፤ በለመዱት የማሳዘን ተግባር ይቀጥላሉ። ለምን ቢባል ብዙ ጊዜ ኅሊናችንን ተጋፍተን የምንዋሽና የምናታልል ከሆነ ከዚያ በኋላ ክፉ ሥራ ስንሠራ አካላችን መሳቀቁንና መደናገጡን ያቆማል፤ ምክንያቱም ከብዙ መሳቀቅ በኋላ <u>ኅሊናችን ክፉ ሥራን ስለሚለማመደው</u> ነው። ቅዱስ ጳውሎስ፣ "ለማያምኑ ግን ንጹሕ የሆነ ምንም የለም፥ ነገር ግን አእምሮአቸውም ሕሊናቸውም ረክሶአል" (ቲቶ 1፡15) ያለው ስለዚህ ነው። እናም ኅሊናቸው የደነዘዘና ክፉና በጎን በሚገባ አመዛዝኖ መለየት የተሳናቸው ሰዎች፡-

- ጥፋት ፈጽመናል ብለው አያምኑም፤

- ይቅርታ ለመጠየቅ ወይም ንስሐ ለመግባት የተዘጋጁ አይደሉም።

ስለዚህ "በእግዚአብሔርና በሰው ፊት ሁልጊዜ ነውር የሌለባት ሕሊና ትኖረኝ ዘንድ እተጋለሁ" (የሐዋ 24:16) የሚለውን የሐዋርያውን ቃል እያሰብን ለሰው ሳይሆን ለኅሊናችን ብለን ከመዋሸት፣ ከማታለልና ሰውና እግዚአብሔርን ከሚያሳዝን ክፉ ሥራ መቆጠብ፣ ጥፋት ፈጽመን ስንገኝም ሰው በእኛ ላይ ከመፍረዱ በፊት ቶሎ ብለን ይቅርታ መጠየቅ አስተዋይነት ነው።

*ለ) ቃለ እግዚአብሔር (አምላካዊ ሕግ)፣*

የሰው ልጅ ስለ ደግነትና ክፋት፣ ስለ ጽድቅና ኃጢአት ያስተማረው ባይኖርም በተፈጥሮ ኅሊናው ያውቃል። ነገር ግን ሰው ለኅሊናው አልታዘዝም ብሎ ሰውና እግዚአብሔርን በሚያሳዝን ተግባር ላይ በመሠማራቱ የሚታይና በጽሑፍ ላይ የተቀመጠ አምላካዊ ሕግ ተዘጋጅቶለታል። ይህንም አምላካዊ ሕግ የሚያስፈጽሙና ሰው ወደ በጎ ሰውነቱ እንዲመለስ የረከሰ (የተበላሸ) ኅሊናውን እንዲቀድስ የሚያስተምሩ ነቢያት፣ ሐዋርያትና የእነሱን አሰረ ፍኖት የሚከተሉ ካህናት ተመድበውለታል። በየዕለቱ በመድረክ ላይ የሚዘራው የሕይወት ቃል የእግዚአብሔርን ዘለዓለማዊ መንግሥት፣ አዳኝነቱንና ሚዛናዊ ፍርዱን የሚያሳውቅ፣ የሰው ልጅ ከክፋት ወደ ደግነት እንዲመለስ የሚያዘክር የድኅነት አዋጅ ነው። እናም በሕይወተ ሥጋ ሳለ በጀሮው የሚሰማውን የፈጣሪን ሕግ ወደ ጎን ትቶ፣ ኅሊናውን ተጋፍቶ በደል የፈጸመ ሰው በሕይወተ ሥጋ ሳለ በዚህ ዓለም፣ ከሞትም ባሻገር በወዲያኛው ዓለም ተደራራቢ ፍርድ ይጠብቀዋል።

*የአምላክን ሕግ ለሚተላለፉ ሰዎች የሚሰጥ ቅጣት፤*

*1) በዚህ ዓለም (በሕይወተ ሥጋ )፤*

የአምላክን ሕግ ተላልፎ ሰውና እግዚአብሔርን በሚበድል ሰው ላይ የጥፋተኝነት ስሜት (ጊልት ኮንሸስ) የወለዳቸው ከላይ የዘረዘርናቸው የሥነ-ልቡና ስብራት ምልክቶች ማለትም ፍርሃትና ድንጋጤ፣ ሞገስ ማጣት፣ ድብርትና ጭንቀት እንዲሁም ራስን ማጥፋት በሕይወቱ ላይ ይንጸባረቃሉ። ይህን አባባላችን እንደሚከተለው በአራት የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃዎች እናረጋግጣለን።



- የአዳም ልጁ ቃየን ወንድሙን አቤልን ከገደለ በኋላ "ምን አደረግህ? የወንድምህ የደሙ ድምፅ ከምድር ወደ እኔ ይጮኻል...በምድርም ላይ ኰብላይና ተቅበዝባዥ ትሆናለህ" (ዘፍ 4:10-12) የሚለውን የፈጣሪ የቁጣ ቃል በመስማቱ የሚያስቃይ ክፉ የጭንቀት በሽታ አድሮበታል። በዚህም ምክንያት ቃየን "ኃጢአቴ ልሸከማት የማልችላት ታላቅ ናት... በምድርም ላይ ኰብላይና ተቅበዝባዥ እሆናለሁ፤ የሚያገኘኝም ሁሉ ይገድለኛል" (ዘፍ 4:14) ሲል መሬቱን፣ ኃዘኑንና ጭንቀቱን ገልጿል።

- በተመሳሳይ ሁኔታ የእስራኤላዊያን ቀዳማዊ መሪ የነበረው ንጉሥ ሳኦል በነቢዩ በሳሙኤል አማካኝነት የተላለፈለትን አምላካዊ ትዕዛዝ እያወቀ ካፈረሰ በኋላ የፈጸመው በደል ኅሊናው ሊቆጣጠርው ከሚችለው በላይ በመሆኑ ለድብርት (ዲፕረሽን) በሽታ ተጋልጧል፤ ክፉ መንፈስም አድሮበታል። ከያዘው በሽታ ዕረፍት ያገኝ ዘንድ በገና በመደርደር የታወቀ ባለሙያ ዳዊት ተፈልጎ ያዝናናው ነበር። "እንዲህም ሆነ ከእግዚአብሔር ዘንድ ክፉ መንፈስ በሳኦል ላይ በሆነ ጊዜ ዳዊት በገና ይዞ በእጁ ይመታ ነበር ሳኦልንም ደስ ያሰኘው ያሳርፈውም ነበር፥ ክፉ መንፈስም ከእርሱ ይርቅ ነበር" (1ሳሙ 16:23) ተብሎ በቅዱስ መጽሐፍ እንደተጠቀሰ። ከዚህም የተነሳ የአእምሮ በሽታ ባለሙያዎችና መንፈሳዊያን የሥነ-ልቡና አማካሪዎች ሙዚቃ (መንፈሳዊ መዝሙር) ክፉ መንፈስ ላደረባቸውና የጭንቀትና የድብርት በሽታ ለሚያሰቃያቸው ሰዎች ዓይነተኛ መፍትሔ እንደሆነ ይናገራሉ።



- የባቢሎን ንጉሥ ታላቁ ሰው ናቡከደነፆር ሥልጣን ከእግዚአብሔር የሰጠው መሆኑን ረስቶ "ይህች እኔ በጉልበቴ ብርታት ለግርማዬ ክብር የመንግሥት መኖሪያ እንድትሆን ያሠራኋት ታላቂቱ ባቢሎን አይደለችምን?" (ዳን 4:30) ብሎ በመናገሩና ከፈጣሪው ጋር በመገዳደሩ ራሱን የሚያስት በሽታ አድሮበታል፤ ተፈጥሯዊ ገጽታው ሁሉ ተለውጦ፣ ኅሊናውን ስቶ፣ ከቤተ መንግሥቱ ወጥቶ ተሰዶ ከአራዊት ጋራ ለሰባት ዓመታት ያህል እንደ እንስሳ ሣር እየበላ ኖሯል። ወደ ልቡናው የተመለሰው ንስሐ ከገባ በኋላ ነበር።

- ከቅዱሳን ሐዋርያት መካከል አንዱ የነበረውና ይልቁንም የገንዘብና የንብረት ክፍል ኃላፊነት የተሰጠው የአስቆሮቱ ይሁዳ ልቡ በፍቀረ-ነዋይ ሰክሮ በየዕለቱ የሚሰማውን የሕይወት ቃለ ወደ ጎን በመተው ለገንዝብ ሲል ጌታውን ለሞት አሳልፎ በመስጠቱና ንጹሕ ደም በማፍሰሱ ለድብርት (ዲፕረሽን) በሽታ ተጋልጧል። በመጨረሻም የፈጸመውን በደል ኅሊናው ሊሸከመው ባለመቻሉ ተስፋ ቆርቶ ራሱን ማጥፋት (ሱሳይድ መፈጸም) ግድ ሆኖበታል (ማቴ 27:5)።

መልካም ፍሬ ማፍራት የተሳነው አንድ የወይን ግቢ አጥሩ ፍርሶ ግንቦ ተጥሶ የተመደበለት የጥበቃ ክፍል ከቦታው ከተነሳ በኋላ የእንስሳት መራዎጫ የአራዊት መፈንጫ እንደሚሆን ሁሉ፣ ክርስቲያንም የእግዚአብሔርን ሕግ አፍርሶ ኅሊናው ያስቀመጠለትን የሕግ ከለላ ጥሶ በኃጢአት ተግባር ላይ ሲሠማራ የተመደቡለት አቃቢያን መላእክት ከእሱ ይለያሉ። ከእግዚአብሔር ሕግ ይወጣል፤ ኅሊናውም ክፏና በጎውን መለየት ይሳነዋል። ከዚያ በኋላ በተፈጥሮ ሰው ሆኖ ሳለ በተግባር ከእንሳት የማይለይ፣ ለሌላው ሰው ደኅንነት ይቅርና ለራሱም የማይበጅ ለቤተሰቦቹ ሸክም ይሆናል።

## *2) በሚመጣው ዓለም (ከሞት በኋላ)፤*

በአለንበት ዘመን የሰው ልጅ ጽድቅና ኩነኔው፣ ደግናቱና ክፋቱ በምድር ላይ ባሉት የአጃቢዎቹ ብዛትና በሚሰጡት የተጠናከረ ድጋፍ የሚለካ ይመስላል። በልዩ ተባሕትዎ ተውስነው፣ በጾም በጸሎት አጥንታቸው ደርቆ ያለፉ፣ ወይም በተሰጣቸው አምላካዊ ጸጋ አጋንንትን በማስወጣትና በመፈወስ የሚታወቁ፣ ወይም ለእምነታቸው ሲሉ መተኪያ የሌላት ውድ ሕይወታቸውን ሰውተው በሰማዕትነት ያለፉ ታማኝ አገልጋዮች ከሞቱ በኋላ ስማቸው አይወሳም። በተቃራኒው ግን ብዙ ወገንና ተከታይ ያላቸው ሰዎች በመንፈሳዊ ሚዛን ወይም በቀኖና ሊለካ የሚችል የጽድቅ ሥራ ሳይኖራቸው ስማቸው ገኖ ታቦት ይቀረጥላቸው እስከ መባል ይደርሳል። እግዚአብሔር ግን ፊት አይቶ የማያዳላ ትክክለኛ ፈራጅ በመሆኑ የሁለቱንም ሥራ በማያዳላ ሚዛኑ ለክቶ እንደየሥራቸው ዋጋቸውን ይከፍላል።

ከዘለዓለማዊ ፍርድ ለማምለጥ ሰው ከሁሉ አስቀድሞ ለአምላክ ሕግና ለሕሊናው መገዛት አለበት። እግዚአብሔርን የሚያከብርና ለኅሊናው የሚገዛ ሰው  ሰውን ይወዳል (ያከብራል)፤ ኃጢአትን ይፈራል፤ እውነትን ይናገራል። እንግዲህ የደግነት መለኪያው ሚዛኑ ይህ ብቻ ነው። ደግነትና እውነተኛነት ካለ ክብርና ዝና ሳይፈልጉት ይመጣል። ይሁዳ በነፍስም በሥጋም የተፈረዳበት የጌታን ንጽሕ ደም በማፍሰሱ ብቻ ሳይሆን፣ ገንዘብ ወዳድ፣ ውሸታምና አታላይ በምሆኑ ጭምር ነው። ጌታን ለማስያዝ አይሁድን አስከትሎ ሲሄድ ዝቅ ብሎ የክርስቶስን ጉልበቱን ስሞታል፤ ጌታ ግን "ይሁዳ ሆይ፥ በመሳም የሰውን ልጅ አሳልፈህ ትሰጣለህን?" (ሉቃ 22:48) ነበር ያለው። በዚህ ዘመን ያለን ሐበሾች በስመ ክርስትና እየኖረን የብዙዎቻችን አንደበት ውሸትን ተለማምዷል። በአጠቃላይ ውሸት ከጓዳ ወጥቶ በአደባባይ ከሚነገርበት፣ እውነት ያለበትን ኃይለ ቃል የሚናገሩ በጥፋተኝነት ከሚፈረጁበት፣ አታላዮችና አስመሳዮች ግን ከሚሸለሙበት ጊዜ ደርሰናል። ነገር ግን ቅዱስ መጽሐፍ ሰው የቤተ ክርስቲያንን ሕግን ሲያፈርስና ውሸትን ሲናገር በቁጣ ቃል መገሰጽ ተገቢ እንደሆነ እንዲህ ሲል ያረጋግጣል፤ "ውሸትን አስወግዳችሁ፥ እርስ በርሳችን ብልቶች ሆነናልና እያንዳንዳችሁ ከባልንጀሮቻችሁ ጋር እውነትን ተነጋገሩ። ተቆጡ ኃጢአትንም አታድርጉ፤ በቁጣችሁ ላይ ፀሐይ አይግባ፥ ለዲያብሎስም ፈንታ አትስጡት" (ኤፌ 4:24)።

እግዚአብሔር ግን እንደ ሰው አይደለም፤ እንደ ቃየን በወንድማቸው ላይ ግፍ የሚፈጽሙ ደም አፍሳሾችና አሳዳጆች፣ እንደ ሳኦል ለቃሉ የማይታዘዙ ሕግ አፍራሾች፣ እንደ ናቡከደነፆር ክብር ፈላጊ ራስ ወዳዶች፣ እንደ ይሁዳ ጥቅም አሳዳጆች የሆኑና ቃሉ ተሸክመው ውሸትን የተለማመዱ የራሳቸውን ኅሊና ገድለው መንፈሳዊ ለመምሰል በማስተማር ወይም መለኮታዊ ሥጋውና ደሙን በማቀበልና በመቀበል የሕዝቡን ልብ የሚያቆስሉ ሰዎች በመጨረሻዋ ቀን የጌታ ዘለዓለማዊ ፍርዱ በእነርሱ ላይ ተፈጻሚ ይሆናል። "ነገር ግን እንደ ጥንካሬህና ንስሐ እንደማይገባ ልብህ የእግዚአብሔር ቅን ፍርድ በሚገለጥበት በቍጣ ቀን ቍጣን በራስህ ላይ ታከማቻለህ። እርሱ ለእያንዳንዱ እንደ ሥራው ያስረክበዋል፤ (ሮሜ 2:5) ተብሎ ተጽፏልና።

"ልጄ ሆይ፥ በክፉ ሰዎች አትቅና፥ ከእነርሱ ጋርም መሆንን አትውደድ ልባቸው ግፍን ታስባለችና፥ ከንፈራቸውም ሽንገላን ትናገራለችና። ቤት በጥበብ ይሠራል፥ በማስተዋልም ይጸናል" (መሳሌ 24:2)።

የልዑል እግዚአብሔር ቸርነት፣ የቅድስት ድንግል ማርያም ምልጃና በረከት፣ የቅዱሳን ተራዳኢነት አይለየን፤ አሜን።

ቀሲስ ዘመነ ደስታ
ሳን ሆዜ
ካሊፎርንያ